# በቃል መርካት

አየ መራብ አይ መጠማት
ቃልን በልቶ በቃል መርካት
ቃል ጠጥቶ በቃል መርካት

ቃል የራበው የወንጌሉ
ቃል የራበው የእየገድሉ
ጣዕም የራበው የጠበሉ
መዓዛውም የዕጣኑ
ዕምነት አጥቶ ከግንባሩ
መስቀል አጥቶ መቾገሩ
ተጠራርቶ ከእየአገሩ
ባንድነት መደመሩ

ቃልን በልቶ ለመርካቱ
ቃል ጠጥቶ ለመርካቱ
ለመተርጎም በሥራ ላይ
ለመደርደር በዋጋ ላይ
ለማሸነፍ ሸንጋይ ደላይ!

ወንጌል ምሉዕ ውቅያኖስ
እረቂቅ ርቁቅ አይደል ትልክስ፡፡
አስተማሪ ሊቃውንቱ
ምስጢር ገልጦ መፈትፈቱ፡፡
እንድንማር ጥንክር ብለን
አውቀን ደምቀን ዕውቀት ኖሮን
እምነት ኖሮን
እንደብረት አጠንክሮን
ልብን ሰጥቶን የልድያን
እንዳይመታን የሐጢዓት ደይን
ዕድል ሰጥቶን የመዳጉን
እንድንሆን ደዌ ፍቱን፡፡
በአሸዋ ላይ ሳንዘራ
በትቢያ ላይ ሳንመራ
እንድንቆም በእበህላዌ
ሳንጠረግ በግሣዊ

አየ መራብ አይ መጠማት
ቃልን በልቶ በቃል መርካት
ቃል ጠጥቶ በቃል መርካት

ከወ/ት አፎሚያ ሚካዔል
ኦስሎ ኮንፍራንስ
ሰኔ 20 ቀን 2000 ዓ:ም